# በርጩማማ ጠፍቷል!

ሀማ ቱማ

ዝም በሉ ይሉናል በርጩማን አታንሱ
ሱቅ በሉ ይሉናል ሂስን አታቅርቡ
ሕዝባዊ ነን ያሉት አፄነት ከጅለው
ዘመናዊ ራሶች ዶክተር ፕሮፌሰር ኤንጂነር ተብለው
ለዴዴሳ እሮሮ ጆሮአቸውን ዘግተው
ሽብሬን ረስተው
ዝዋይ ሽዋ ሮቢትን ጭራሹን ዘንግተው
ታሪክ ተመክሮን ከትቢያ ደባልቀው
ከወያኔ ጫማ ሳያፍሩ ተደፍተው
ምርጫ ገባን ያሉ
ልናሸንፍ ብለው ስንቱን ያጃጃሉ
በርጩማ ስትጠፉም ቀጠሮ አምስት ዓመት ብለው የሰበኩ
ለአረመኔው መለስ  አሻንጉሊት ሆነው ትግልን ያዳከሙ
ወቀሳ ይነሳቸው፤ አጠፉችሁ መባል
መነገር መርዶውን በርጩማውም ጠፍቷል?
ይወገራል እንጂ ምነው አይወገር
ይወቀጣል እንጂ ምነው አይወቀጥ
ይወቀሳል እንጂ ምነው አይወቀስ!
ባንዳን ባንዳን ማለት ወየት ነው ኃጢያቱ
ሕዝብ ፊት ሲጋለጥ ያ ፀያፍ ክህደቱ?
መካሪ ሳይጠፉ ስህተትን ሲደግሙ?
ተዉን እንናገር ከብራችን አይጥፉ
ወያኔ ሲለፍፍ ሲጮህ ሲደነፋ
ጉንፋን አንበለው ቀሳፊውን በሽታ!
እውነቱ ይነገር ጠዋትና ማታ
መዋረድ መጎንበስ የአድር ባይ ልፈፋ
ቅሌት መከናነብ ላይገኝ በርጩማ!